# ሞረሽ ወገኔ የተባለውን ጠባብ ዘረኛ
# እንቃወማለን

## የጋራ መግለጫ

ጥር 18/ 2005

እኛ ከተለያዩ ያማራ ደብሮችና መስጊዶች የተውጣጣን ጊዜዊ ተወካዮች ሞረሽ ወገኔ የተባለው የማናውቀው ቡድን ስለአስቀየመን የኢትዮጵያ ሕዝብ በቡድኑ ላይ ያለንን ተቃውሞ እንዲያውቅልን ብለን ተመካክረን የሚከተለውን መግለጫ እንድሰማልን ተስማምተናል ።

ሞረሽ ወገኔ የተባለው እኛ አማሮች የማናውቀው የማንፈልገው ባእድ ነገር ነው ።ስራው ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ጋር የሚያአጣ ክፉ ስራ ነው ። በአማራው ስም ተቆርቋሪ ነኝ እያለ የሚአወጣው ወረቀት ሁሉ እኛን ዘረኛና ጠባብ ተደርገን እንድንታይ ስለአደረገን በጣም አሳዝኖናል ።

ሁሉ እንድያቅልን የምንፈልገው ሞረሽ ወገኔ የተባለው ከአማራው ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውና አማራውም የማይፈልገው ስለሆነ በጥብቅ እናወግዘዋለን እንቃወመዋለን ።

አማራው ኢትዮጵያዊ ነው ። በራሱ ላይ የሚደርስበትን መከራ ሁሉ በኢትዮጵያዊነት ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ ጋር በእግዚአብሔር ድጋፍ ይወጣዋል ። ወገኑና አጋሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሆነ ኢትዮጵያዊነቱን እየካዱ ጠባብ እያደረጉ በስሙ በቡድን የሚደራጁና  የሚነግዱ ሞረሽ ወገኔንና ሌሎችንም ጠባብ ዘረኞችን ሁሉ እናወግዛለን

የአማራ ጊዜዊ ተወካዮች